DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

January 2018

ውድ የኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማኅበረሰብ፣

ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) ስለ ኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (CoolidgeCoolidge High School) መርሀ ግብር እቅዶች ለእናንተ ለማካፈል በጣም ደስተኛ ነው። በ 2019-2020 የትምህርት ዓመት፣ ኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በሦስት የአካዳሚክ ዘርፎች ላይ የሚያተኩር፣ ማለትም በጤና ሣይንስ ዘርፍ፣ በብዙኃን መገናኛ እና ቀደም ባለ አዲስ አማራጭ መርሀ ግብር አማካይነት በአዲሱ ሕንጻ ውስጥ ይከፈታል።

ኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዳበረ ታሪክ አለው። በዚህ በዳበረ ታሪክ ላይ፣ ለኩሌጅ (Coolidge) የወደፊት እድል እቅድ ለመንደፍ ደስተኞች ነን። በተጨማሪም ለዲሲ ተማሪዎች ወላጆች፣ በተለይም ለቀጠና 4 ተማሪዎች ወላጆች ኩሌጅ እየጎለበተ በመስፋፋት የሚዝዙ አማራጮች ሆኖ የሚቀጥል መሆኑን ዕውን ለማድረግ ለኩሌጅ የወደፊት እቅድ ለመንደፍ ደስተኞች ነን።

ዲሲፒኤስ ከኩሌጅ ማኅበረሰብ ጋር በመሆን፣ በወላጆች፣ በመህራን፣ በተማሪዎች ተኮር ቡድኖች፣ በማኅበረሰብ ስብሰባዎች እና እንዲሁም በኦንላይን (online) አሰሳ መጠይቆች አማካይነት፣ ስለ ኩሌጅ እና ስለ አዲሱ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እቅዶች ለመንደፍ አንድ ላይ በመቀናጀት ተሰልፏል። የእነዚህ አካዳሚዎች የወደፊት እጣ እድል መልክ የሚይዘው ቀጥታ ከኩሌጅ ማኅበረሰብ ጋር አንድ ላይ ለመሥራት በሚደረግ ጥረት ነው። የተረዳነውም ከዚህ በታች እንደ ተመለከተው ነው።

- ማኅበረሰቡ በአሁኑ ጊዜ በኩሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Coolidge) ስለሚገኙት የብዙኃን መገናኛ ዘዴዎች እና የጤና ሣይንስ አካዳሚዎች በከፍተኛ ዕሴት የሚመለከታቸው ሲሆን እነዚህ መርሀ ግብሮች በትምህርት ቤቱ ክልል ለሚገኙ ነዋሪዎች የተማሪዎች ወላጆች እጅግ በጣም ጥሩ የሆኑ የአካዳሚክ እድሎች ለልጆቻቸው እንዲያቀርቡ ስለሚፈልጉ ክፍት ሆነው እንዲኖሩ ይፈልጋሉ።

- ወላጆች፣ ተማሪዎች፣ እና መምህራን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በመመራመር ዕውቀትን እና ጽንሰ ሀሳቦችን ለሚያስ ጨብጡ ብርቱ ሥራዎች በርካታ አማራጮችን ይሻሉ። ይህንን በሥራ ላይ ሆነን የሰማነው ሲሆን፣ በተጨማሪም በምዝገባ መረጃዎቻችን አማካይነት ተመልክተነዋል። ይህም በመቶዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች ከኩሌጅ ትምህርት ቤት ክልል፣ ከቀጠና 4 ውጪ የሚገኙ የዲሲፒኤስ የምርጫ ትምህርት ቤቶችን ወይንም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ በሌሎች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይማራሉ።
- የተማሪዎች ወላጆች እና መምህራን ስለ ዳበረ እና ስለበለጸገ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርት ገጠመኝ ልምዶች ደስተኞች ናቸው። አዲሱ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጋር የተቆራኘ እንዲሆን የሚፈልጉ ሲሆን፣ በተጨማሪም በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ፍላጎቶች ላይ የሚያተኩሩ ልዩ ትምህርት ቤቶች እንዲሆኑ ይፈልጋሉ።

ይህን ራዕይ እውን ለማድረግ በሚደረግ ጥረት የኩሌጅ (Coolidge) ትምህርት ቤቶች ዘርፎች፣ ለኩሌጅ ማኅበረሰብ እና ለከተማ አቀፍ ነዋሪዎች በርካታ ጥራት ያላቸው የመርሀ ግብር አማራጮች ያቀርባሉ።

**የጤና ሣይንሥ አካዳሚ፤ (Health Sciences Academy)**

- የክልል እና የመጋቢ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመመዝገብ መብቶች አሏቸው፤
- የአካዳሚክ ትምህርቶች እድገት የሚቀጥል ሲሆን የመንታ ምዝገባዎች ተጓዳኝነት እንዲቋቋም ይደረጋል፤
- ለመንታ ምዝገባ እድሎች እና የፋኩልቲ መምህራን ቅንጅቶች የሣይንስ አማራጭ ኮርሶች የዩንቨርሲቲ ተጓዳኝነቶች ይኖራሉ፤
- በኢንዱስትሪ ቦርድ፤ ንግግር በሚያደርጉ ተጋባዦች የቦታዎች ጉብኝቶች እና የፋኩልቲ ቅንጅት እና ለሚሠለጥኑ ገንዘብ በሚ ከፍሉ የሙያ ላይ ማሠልጠኛዎች አማካይነት የሙያ ላይ ድጋፍ ቅንጅቶች እና፣
- የረዳት ነርስነት እና የመጀመሪያ የጤና አገልግሎት የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች።

**የብዙኃን መገናኛ አካዳሚ (Mass Media Academy:)**

- የክልል እና የመጋቢ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመመዝገብ መብቶች አሏቸው፤
- በጤና ሣይንስ አካዳሚ ሞዴል የተቀየሰ የሙያ አካዳሚ መርሀ ግብር፣
- በጋዜጠኛነት እና በማምረቻ እንዲሁም በዩንቨርሲቲ ቅንጅት አማራጭ ለመንታ ምዝገባ እድሎች፣

- በኢንዱስትሪ ቦርድ፣ ንግግር በሚያደርጉ ተጋባዦች፣ የቦታ ጉብኝዎች እና በሚከፈላቸው የሙያ ላይ ሥልጠናዎች አማካይነት የሙያ ላይ ድጋፍ ቅንጅቶች፤ እና
- ቪዲዩ እና ሲኒማዎችን የማረሚያ እና ማስተካከያ፣ እንዲሁም የሚንቀሳቀሱ የንግድ ማስታወቂያዎችን የመሥራት ጥበብ የሙያ ብቃት የምስክር ወረቀት (Adobe Premier Pro and After Effects certifications.)

**የመጀመሪያ ደረጃ የኮሌጅ አካዳሚ (Early College Academy)**

- በትምህርት ቤቴ ዲሲ የሎተሪ ዕጣ አማካይነት ከተማ አቀፍ የማመልከቻ ፕሮግራም፤
- ከ 2019-2020 የትምህርት ዓመት ከ9 ንኛ ክፍል ጀምሮ፣ ፕሮግራሙ ያድጋል፣ እንዲሁም፤
- የላቁ የክፍል ምደባ እድሎችን ጨምሮ ቅድሚያ በመስጠት የ 9 እና 10ኛ ክፍሎች ኮርሶች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርት የሚሰጥባቸው ይሆናሉ። የ 11ደኛ እና የ 12ተኛ ክፍሎች ኮርሶች በ 12ተኛ ክፍል ማብቂያ ላይ በዩንቨርሲቲ መልክ መሠረት እስከ 60 ክሬድቶች (credits) የሚያሰጡ የኮሌጅ ኮርሶች ይሆናሉ።

ሦስቱም የትምህርት ደረጃዎች፣ የተቀናጁ፣ ከዐላማ ጋር የሚጓዙ እና የተዋኻዱ የትምህርት ባህል ያላቸው ሆነው እንዲገኙ በበላይነት የሚመራ አንድ ርእሠ መምህር እና በተጨማሪም እያንዳንዱ አካዳሚ የየራሱ ርእሠ መምህር ይኖረዋል። መለስተኛው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የራሱ ርእሠ መምህር እና የተለየ የመግቢያ በር፣ እንዲሁም የተለዩ የመማሪያ ክፍሎች የሚኖሩት ይሆናል። መለስተኛው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ 2019-2020 የትምህርት ዓመት 6ተኛ ክፍል በመክፈት፣ ክፍል በክፍል እያደገ ይሄዳል። ራዕያችን የመለተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ከሦስቱ የትምህርት ቤት ደረጃዎች በአንዱ ትምህርቶቻቸውን ስኬታም ለማድረግ ዝግጁ ሆነው ኩሌጅ (Coolidge) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደሚገቡ ነው። የኩሌጅ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሁሉ፣ በትምህርት ቤቱ የሚሰጧቸው ትምህርቶች፣ በርካታ ገጠመኞች እና እድሎች እንዲኖሯቸው እና ለኮሌጅ ትምህርቶችም ዝግጁዎች ሆነው እንዲገኙ እውን በማድረግ ለኮሌጅ ትምህርት እና ለሙያ ዝግጁ እንደሚያደርጋቸው እናምናለን።

ለአካዳሚክ ትምህርቶች ድጋፍ የሚያደርጉ የዩንቨርሲቲ እና የማኅበረሰብ ተጓዳኝነቶችን ለማቀናጀት በመጭዎቹ ጥቂት ወራት ዲስፒ ኤስ እየጎለበተ መጓዙን የሚቀጥል ሲሆን፣ ኣነዚህ ወቅቱን ጠብቀው ስለሚካሄዱ ጥረቶች የመጨራሻ ደረጃቸው ላይ ስለመድረስ ለማኅበረሰብ ለማካፈል እንወዳለን። በተጨማሪም ከኩሌጅ ወላጆች እና ተማሪዎች ጋር የበለጡ መረጃዎችን በጋራ መለዋወጥ የምንችልበትን ጊዜ ለማመቻቸት ከርእሠ መምህር ብራይት (Bright) ጋር አብረን እንሠራለን። በዚህ ጉዳይ ላይ የበለጡ ዝርዝሮችን ለማግኘት በመጭዎቹ ሣምንታት እባክዎን ይመልከቱ።

እስከ አሁን ድረስ በዚህ ሂደት ውስጥ ለአድረጉት አስተዋጽዖ እያመሰገንን፣ በኩሌጅ (Coolidge) እና በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በሁለቱም ስለሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞችን ስለመንደፍ እና ተግባር ላይ ሰለማዋል በመጭዎቹ ወራት ሥራችንን ከእርስዎ ጋር ለምሥራት በጉጉት እየተጠባበቅን እንገኛለን። በዲሲፒኤስ የትምህርት ቤት እቅዶች ብሎግ (blog) http://bit.ly/coolidgeplanning, ላይ ስለዚህ ሂደት የበለጠ ሊገነዘቡ ይችላሉ፤ ወይንም በዚህ ሂደት ላይ እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ ለማወቅ የእቅድ ቡድኑን በ DCPS.Planning@dc.gov አማካይነት ማነጋገር ይችላሉ።

ከልባዊ ሠላምታ ጋር፣

Wanda H. Legrand, Ed.D
Deputy Chancellor
Social Emotional Academic Development